በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.98
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.98

# ኤጀንሲው የድሬዳዋ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትና የጫት ላኪዎች ማኅበር ህንፃ እንዲመለስ የመጨረሻ ውሳኔ አሳለፈ

የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ቦርድ በደርግ መንግስት መንግስት ተወርሶ በአሁን ሰዓት የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የያዘውን ባለ አራት ፎቅ ህንፃ ለባለንብረቶቹ ለድሬዳዋ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትና ለኢትዮጵያ ጫት ላኪዎች ማኅበር እንዲመለስ የመጨረሻ ውሳኔ መጋቢት 18 ቀን 2007ዓ.ም. አሳለፈ፡፡



*አቶ የወንድወሰን ዘለቀ(የድሬዳዋ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት)*

የጠቅላይ ሚንቴር ጽ/ቤት ሐምሌ 29 ቀን 2006ዓ.ም. ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ግንቦት 30 ቀን 1994 ጫ.ም. በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 4/2/ሐ እና በአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 01//88 በተደነገገው መሰረት በመርህ ደረጃ ለባለመብቶቹ እንዲመለስ በወሰናችሁት መሰረት እንዲፈፀም ብሎ ደብዳቤ መፃፉ የሚታወስ ሲሆን የአፈፃፀም ሂደቱ ሲጓተት እስካሁን እልባት ሳያገኝ ቆይቷል፡፡

ለዚህም ዋንኛው ምክንያት ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ መንግስት ለድሬ ኤፍ ኤም ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን እንዲሁም ለድሬዳዋ ም/ቤት ህንፃውን እየተገለገለበት እንደሆነና ከፍተኛ ወጪ ስላወጣበት በመሆኑ ለባለንብረቶቹ ካሳ ተከፍሎ ህንፃውን ለግሉ ያስቀረው የሚል ሌላ ሀሳብ አቅርቦ ውሳኔ ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

ይሁንና የጠቅላይ ሚንስቴር ጽ/ቤት ለሁለተኛ ጊዜ ጥቅምት 13 ቀን 2007ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ ንብረትነቱ የድሬዳዋ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትና የኢትዮጵያ ጫት ላኪዎች ማኅበር መሆኑን አስረግጦ በመግለፅ ለህንፃው ማስፋፊያ ወጪ ተደርጓል የተባለው ገንዘብ ተሰልቶ ባለንብረቶቹ እንዲከፍሉና ንብረታቸውን እንዲረከቡ፣ መክፈል ካልቻሉ ደግሞ አስተዳደሩ ተገቢውን ካሳ ከፍሎ ለህንፃ መስሪያ ተለዋጭ ቦታ እንዲሰጣቸው በወሰነው መሰረት ለመፈፀም ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡የድሬዳዋ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ የወንድወሰን ዘለቀ ለኢትዮ-ቻምበር እንደገለፁት ምክር ቤታቸው የተጠየቀውን ብር ከፍሎ ህንፃውን ለመረከብ መዘጋጀቱን ገልፀው ምናልባትም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ህጋዊ ጉዳዮችን አጠናቅን ንብረታችንን በእጃችን እናስገባለን ብለዋል፡፡

አድራሻ/ፋክስ: - +251-011-5517699
ኢ.ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ:- www.ethiopianchamber.com

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.98
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.98

"ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ለዚህ ስኬት በቅተናል:: ውሳኔው መንግስት ለንግዱ ማኅበረሰብ ያለውን አጋርነት ያረጋገጠበት ነው" ሲሉ አቶ የወንድወሰን የተሰማቸውን ደስታ ለኢትዮ-ቻምበር ገልፀዋል::

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባዔ ሚያዚያ 30 ቀን 2006ዓ.ም. በሸራተን ሆቴል ባካሄደበት ወቅት የድሬዳዋ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ህንፃ ጉዳይ ለጠቅላይ ሚንስቴር ጽ/ቤት እንዲቀርብ አቶ የወንድወሰን ጥያቄ ማቅረባቸው የሚታወስ ሲሆን ጥያቄያቸው በጠቅላላ ጉባኤውና በምክር ቤቱ አመራር አካላት ተቀባይነት አግኝቶ እንደነበር ይታወሳል::

"በዚህ አጋጣሚ ለዚህ ስኬት እንድንበቃ በተለይ የቀድሞው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቀድሞውና የአሁኑ አመራር አካላት በአጠቃላይ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት የምክር ቤታችን ህንፃ እንዲመለስ ላደረጉልን ከፍተኛ እገዛ በእጅጉ እናመሰግናለን" ሲሉ አቶ የወንድወሰን የተሰማቸውን ደስታ ገልፀዋል::

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተሸለመ

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በግሉና በመንግስት የምክክር መድረክ በተካሄዱ ውጤቶች መጋቢት 6 ቀን 2007 ዓ.ም. በዴንማርክ ኮፐንሀገን ከተማ በተካሄደው 8ኛው ዓለም አቀፍ የምክክር መድረክ ኮንፈረንስ ከ54 አገሮች ጋር ተወዳድሮ ዓለም አቀፍ የክብር ሽልማት አሸናፊ ሆነ::

በዴንማርክ ኢንዱስትሪዎች ፌዴሬሽን አዘጋጅነት የተካሄደው አለም አቀፍ የምክክር መድረክ ኮንፈረንስ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ያሸነፈው የግሉን ዘርፍ ችግር ለመፍታት ባደረገው ከፍተኛ ጥረት ውጤቶች የተገኙበት የምክክር መድረኮችን በብቃት ማዘጋጀት በመቻሉ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል::

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰሎሞን አፈወርቅ ሽልማቱን ከተቀበሉ በኋላ ባደረጉት ንግግር ምክር ቤቱ ለዚህ ስኬት መብቃቱ ለግሉ ዘርፍ እጅግ ጠቃሚ ሲሆን በቀጣይ ከመንግስት ጋር ለሚደረጉ የምክክር መድረኮች ስኬታማነት የላቀ ድርሻ ይኖረዋል ብለዋል::

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የምክክር መድረክ ከጉንስሱ ጀምሮ የዓለም ባንክ ግሩፕ ድጋፍ እንዳልተለየው የሚታወቅ ሲሆን በሽልማት ስነ ስርዓቱ ላይ በዓለም ባንክ ግሩፕ የዓለም አቀፉ የፋይናንስ ተቋም በኢትዮጵያ ስራ አስኪያጅ አቶ ማሞ ምህረቱ የብዙ ዓመታት ድካም ዛሬ ውጤት አግኝቶ አይተናል ሲሉ የተሰማቸውን ደስታ ገልፀዋል::

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.98
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.98

የሽልማት ኮሚቴው ከዴንማርክ ኢንዱስትሪዎች ፌዴሬሽን፣ ከዴንማርክ የውጭ ጉዳ ሚንስቴር ፣ ከዓለም ባንክ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፣ ከዓለም አቀፉ የግል ኢንተርፕራይዞች ማዕከል እና ከገለልተኛ የምክክር መድረክ ባለሙያዎች የተውጣጣ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡




የኢትዮጵያ ግሉና የመንግስት የምክክር መድረክ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ አቶ እዮብ ተካልኝ የምክክር መድረኩ ስኬት መንግስትና የግሉ ዘርፍ በጋራ ያገኙት በመሆኑ ሁላችንንም የሚያስደስት ነው፡፡ ሁለቱ ጠንክረው ባይሰሩ ዛሬ ያገኘነው ውጤት የማይታለም ይሆን ነበር ብለዋል፡፡

## በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚሰጡ የግል ሥራ ፈጠራ ሥልጠናዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ተገለፀ

በጀርመን የፌዴራል የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ሚኒስቴር ( BMZ) የፋይናንስ ድጋፍ ሰጭነት የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተመድበው ለሚማሩ ተማሪዎቹ በተጨማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ለ5 ወራት በሙከራ (PILOT) ደረጃ የተሰጠውን አንተርፕሩነርሽፕ የትምህርት ፕሮግራም (Applied Entreprenurship Education Pro-gramme ) ማጠናቀቂያ ምክንያት በማድረግ ከአገር ውስጥ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እና የፋይናንስ ድጋፉን የሚያደርገው ሚኒስቴር መ/ቤት ባለሥልጣናት በተገኙበት የአንድ ቀን አውደጥናት በሞናርክ ሆቴል /አዲስ አበባ / መጋቢት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ተካሂዷል ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በመላ የኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢ መንደሮች በመጠነኛ ዋጋ ሊዳረስ የሚችል በባለጎማ ጋሪ ላይ የተገጠመ እና በፀሐይ ብርሃን ኃይል ተሞልቶ በአገልግሎት ላይ የሚውል በፀሃይ ብርሀን የሚሰራ (ሶላር ዋገን) የቡድን የፈጠራ ሥራ ውጤት ምስል እና በፓዎርፖይንት የተደገፈ ገለጻ ተደርጓል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በመላ የኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢ መንደሮች በመጠነኛ ዋጋ ሊዳረስ የሚችል በባለጎማ ጋሪ ላይ የተገጠመ እና በፀሐይ ብርሃን ኃይል ተሞልቶ በአገልግሎት ላይ የሚውል በፀሃይ ብርሀን የሚሰራ (ሶላር ዋገን) የቡድን የፈጠራ ሥራ ውጤት ምስል እና በፓዎርፖይንት የተደገፈ ገለጻ ተደርጓል፡፡

አድራሻ/ስልክ: - +251-011-5517699
ኢ-ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ:- www.ethiopianchamber.com